DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS



www.dcps.dc.gov

ጥያቄዎች አሉዎት? በቀጣዩ አድራሻ ያግኙን
(202) 719-6613 ወይም ofpe.info@dc.gov.

1200 First Street, NE, Washington, DC 20002

/dcpublicschools @dcpublicschools @dcpublicschools

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የወላጅ ስርዓተ ትምህርት መምሪያ



# የክፍል ደረጃ 6




# የወላጅ ስርዓተ ትምህርት መምሪያ የአጠቃቀም መንገድ፡

ይህ መምሪያ ልጅዎን በቤት ውስጥ ለማገዝ የሚያስፈልጉዎትን መሳሪያዎች ይሰጥዎታል። በዚህ የመረጃ ጥራዝ ውስጥ፣ ልጅዎ የትምህርት ግቦቹን እንዲያሳካ ለማገዝ እንዲችሉ በ DCPS ስርዓተ ትምህርት ላይ የተመሰረቱ ስትራቴጂዎችን ያገኛሉ። ልጅዎ በት/ቤት ውስጥ የሚማረውን ትምህርት እና በተጨማሪም በቤት ውስጥ እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ጥሩ ግንዛቤ ይጨብጣሉ/ያገኛሉ።

## እርስዎ ማድረግ የሚችሉት፡

በልጅዎ አካዳሚክ ብቃት ላይ እርስዎ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በቤት ውስጥ ጥሩ ትምህርት እንዲያገኙ ለማድረግ እነዚህ የተወሰኑ አስፈላጊ ነጥቦች ናቸው፡

- ትምህርት የስኬት መሰረት መሆኑን ልጅዎ እንዲያውቅ ያድርጉ።
- ልጅዎ 6ኛ ክፍል ውስጥ ምን ይማራል ተብሎ እንደሚጠበቅ ይወቁ።
- ልጅዎ ከፍተኛ የሆኑ የአጭር ጊዜና የረዥም ጊዜ አካዳሚያዊ ግቦችን እንዲያሰቀምጭ ያግዙት።
- የቤት ስራ በተገቢው ሰአት እና በአግባቡ እንዲያጠናቅቅ በቂ ጊዜ ይስጡ።
- በት/ቤት ውስጥ ምን እየተካሄደ እንደሆነ ከልጅዎ ጋር በመነጋገር ሒደታዊ ለውጦችን ያለማቋረጥ ይከታተሉ።
- ለልጅዎ ይሚገቱ።
- የልጅዎን ጥንካሬ ከመምህሩ ጋር ይጋሩ።

## የልጅዎን መምህር መጠየቅ የሚያስፈልጉ ጥያቄዎች፡

ከልጅዎ መምህር ጋር በሚወያዩበት ጊዜ ስለ ልጅዎ የትምህርት አቀባበል እና ሁኔታ ላይ ትኩረት እያደረጉ ቀጥሎ የተመለከቱትን ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፡

- የመማር ግቦች ምንድን ናቸው? የመማር ግብ አስመልክቶ ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች እንደ ምሳሌ ሊነግሩኝ ይችላሉ?
- የልጄን ስራ እንደ ምሳሌ ማየት እችላለሁ? እነዚህን የመማር ግቦች የሚያሳካው ወይም የማያሳካው እንዴት ነው?
- ልጄ በትምህርቱ እያለ/ ከሆነ ደረጃ በላይ ሲዘልቅ ሌላ ተጨማሪ ድጋፍ ማድረግ የሚገባኝ ምንድናቸው? ቤት ውስጥ ምን ማድረግ እችላሁ?
- ቤት ውስጥም መተግበር ያለባቸው የመማሪያ ክፍል ውስጥ መደበኛ ተግባራት ምንድን ናቸው?
- የእርስዎን ክፍለ ጊዜ በተመለከተ ለልጄ በየቀኑ ማቅረብ ያለብኝ ጥያቄዎች ምን ዓይነት ናቸው?

## ከልጅዎ ጋር መነጋገር፡

ጥሩ ጭውውቶች ልጆቻችን በሕይወታቸው ውስጥ እኛ እንደሚያገባን እንዲያዩ ያግዛሉ። እነዚህ ከልጆችዎ ጋር መልካም ውይይት በሚያደርጉበት ጊዜ በቅድሚያ መጠየቅ የሚያስፈልጉ ጥያቄዎች፡

- እስኪ በቀንህ ውስጥ ምርጥ ስለምትለው ጊዜ አውራኝ።
- በውሎህ ውስጥ ያጋጠመህ እጅግ በጣም ፈታኝ ነገር ምንድነው?
- ዛሬ ከተማራችሁት ውስጥ አንድ ነገር ልታሳየኝ ትችላለህ?
- ት/ቤት ውስጥ የምታነቡት መፅሐፍ ምንድን ነው? የምትወደውን መገለጫ ባህርይ ብትነግረኝ? ይህን መገለጫ ባህርይ የምትወደው ለምንድን ነው?
- በት/ቤት ውስጥ ከዚህ በላይ መስራት አለብኝ የምትላቸው ነገሮች ምንድናቸው? በአነስተኛ መጠን ማድረግ አለብኝ ብለህ የምታስበውስ ምንድን ነው? ለምን?

# የስድስተኛ ክፍል ተማሪዬ እየተማረ ያለው ነገር

| | የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት | ሒሳብ | ሳይንስ | ማህበራዊ ሳይንስ |
|---|---|---|---|---|
| የበልግ ወቅት | ተማሪዎች በ Mildred D. Taylor የተደረሰውን *Roll of Thunder, Hear My Cry* የሚል ልቦለድ በማንበብ ለአካለ መጠን መድረስን የሚገልጽ ታሪክ፣ የጀግንነት ምዘና እና ስልታዊ ኢ-ፍትሐዊነትን መዳሰሻ፣ እንደዚሁም በታላቁ መቀዛቀዝ ወቅት በአሜሪካ ደቡብ የነበረውን የዘር ተኮር ግንኙነት በተመለከተ ትችት በሚያቀርብ መልክ ያነብባሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች ልጆች በሚያድጉበት ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች ከግምት ውስጥ ያስገባሉ፣ የዕድገት ሁኔታ በጊዜ ሒደት የቀለለ ስለመሆኑና እነዚህን ተግዳሮቶች ለማቃለል ምን መደረግ እንዳለበትም ጭምር ያያሉ። | ተማሪዎች የጥምርታ ጽንሰ ሃሳቦችን በመረዳት የጥምርታ ምክንያታዊነትን በመጠቀም መልመጃዎችን ይፈታሉ። ተማሪዎች ከዚህ በፊት የነበራቸውን የማባትና የማካፈል ግንዛቤ በመጠቀም ክፍልፋዮችን በክፍልፋይ ያካፍላሉ። ተማሪዎች ባለ ብዙ አሃዝ ቁጥሮችን በመጠቀም ስሌት ማስላትና የጋራ አካፋዮችና ብዜቶችን ያገኛሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች ከዚህ በፊት የነበራቸውን የቁጥር ግንዛቤ በመተግበርና በማስፋት በራሽናል ቁጥሮች ሲስተም ላይ ይተገብራሉ። | ተማሪዎች በመሬት፣ በፀሐይ፣ በጨረቃ፣ በሶላር ሲስተምና በሚልክ ዌይ ጋላክሲ መካከል ያሉትን ግንኙነቶች ያጠናሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች መሬት በቢሊዮን ዓመታት ውስጥ እንዴት እንደተቀየረች ይዳስሳሉ። | የት እንዳለን የምናውቀው እንዴት ነው? በአቅራቢያና በሩቅ ያሉ አካባቢዎችን በመዳሰስ፣ ተማሪዎች ጂኦግራፊ የባህል፣ የፖለቲካዊ መዋቅሮችና ማህበራዊ መዋቅሮችን ዕድገት እንደሚመለከት ይማራሉ።<br>•••<br>አሜሪካ ምንድን ናት? ተማሪዎች በአሜሪካ ውስጥ ያሉ ክልሎችን በመዳሰስ ንግድ፣ ፍልሰትና ሰፈራ የዕድሎችን መጠን በምን ያህል ደረጃ እንደሚጨምር ይማራሉ።<br>•••<br>መካከለኛው ምስራቅ የሚገለጸው በምንድን ነው? ተማሪዎች ሶስቱን የአብርሐም ሃይማኖቶች ይዳስሳሉ፡ አይሁዳዊነት፣ ክርስትና እና እስልምና እመነቶቻቸውንና ጠባዮቻቸውን ማነጻር። |
| የክረምት ወቅት | ተማሪዎች ለዩናይትድ ስቴትስ መሰረት የሆነውን የኢሚግሬሽን ተሞክሮ በተመለከተ በጥልቀት ይመረምራሉ። እነርሱ የሚያከናውኗቸው የትምህርት ተሞክሮዎች ስለ ኢሚግሬሽን አለም አቀፋዊ የሰው ልጅ ተሞክሮ እና በየቀኑ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን የሚመለከት የፖሊሲ ጉዳይ አድርገው በጥልቀት እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል። | ተማሪዎች ከዚህ በፊት የነበራቸውን የአርትሜቲክ ግንዛቤ በአልጀብራዊ አገላለጽ ላይ ተግባራዊ ያደርጋሉ። ተማሪዎች ባለ አንድ ተለዋዋጭ ኢኩዌዥኖችና ኢንኢኩዋሊቲስ በተመለከተ ይፈታሉ። ተማሪዎች በጥገኛና ኢ-ጥገኛ ተለዋዋጮች መካከል አሃዛዊ ግንኙነቶችን ወክለው ይተነትናሉ። ተማሪዎች ስፋት፣ ዙሪያ ልክና መጠንን የሚመለከቱ የተጨባጭ ዓለምና ሒሳባዊ መልመጃዎችን ይፈታሉ። | ተማሪዎች የቀድሞ የጂኦ ሳይንስ ሒደቶች ስለ መሬት ማቴሪያሎችና ተፈጥሯዊ አደጋዎች ምን እንደሚነግሩን ያጠናሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች በአየር፣ በውቅያኖስ እና በመሬት መካከል ያለው ግንኙነት የአየር ሁኔታ አካሄዶችን ለመተንበይ እንዴት ጥቅመ ላይ እንደሚውልና ይህም እውቀት በዓለማችን ላይ እንዴት እንደሚተገበር ይማራሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች የተፈጠሮ ሐብቶች አጠቃቀም በአካባቢ ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ ይዳስሳሉ። | እያንዳንዱን ልጅ የማስተማር ሃላፊነት የማን ነው? ተማሪዎች ጂኦግራፊ በደቡብ ኤዥያ ውስጥ ልጆች ለትምህርት ያላቸውን ተደራሽነት ይመረምራሉ።<br>•••<br>ዓለማችን በከፍተኛ ፍጥነት እያደገች ነው? ተማሪዎች ምስራቅ ኤዥያን በማጥናት ባለፉት ሁለት ክፍለ ዘመናት ውስጥ ፈጣን የዓለም ሕዝብ ቁጥር መጨመር መንስኤና ውጤቶችን ይመረምራሉ።<br>•••<br>አውሮፓ ይበልጥ ሃያል የምትሆነው በጋራ ነው ወይስ በተናጠል? ተማሪዎች የአውሮፓን አካላዊና ሰብአዊ ጂኦግራፊ ይመረምራሉ፣ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ በአውሮፓ ሐብትን ለማሰራጨት ጥቅም ላይ የዋሉትን ዋና ዋና የኢኮኖሚ ስርዓቶች ይተነትናሉ። |
| የፀደይ ወቅት | ተማሪዎች ታሪኮቻቸውን በማጋራት፣ ለሚያምኑበት ነገር በመቆምና እርምጃዎቻቸውን ለማሳወቅ አዲስ ዕውቀት ያለማቋረጥ በመሻት ለማጋራት የሚችሏቸውን የተለያዩ ተሞክሮዎች ይዳስሳሉ። | ተማሪዎች ስለ ስታስቲካዊ ተለዋዋጭነት ግንዛቤያቸውን በማሳደግ ስርጭቶችን የሚያጠቃልሉና የሚገልጹ ይሆናል። | ተማሪዎች የተፈጥሮ ሐብቶች አጠቃቀም በአካባቢ ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ ይዳስሳሉ። | ስለ አፍሪካ በምናወራበት ጊዜ ስለምን እናወራለን? የአፍሪካን ብዝሃነት ያለው የመሬት አቀማመጥ፣ ባህላዊ ጂኦግራፊና ቋንቋዎች በመተንተን ተማሪዎች ስለ አጠቃላይ “አንዲት” አፍሪካ ብቻ መወያየት እንደሌለባቸው ይማራሉ።<br>•••<br>ሃገራት አንዱ ለሌላው ምን ዕዳ አለበት? ተማሪዎች የተፈጥሮ አደጋዎችን መንስኤዎችና ተጽእኖዎች፣ እንደዚሁም የአለም ዜጎች ለእነዚህ ቀውሶች የሚሰጧቸውን ምላሾች ይመረምራሉ። |

# ከስድስተኛ ክፍል ተማሪዎ ጋር የምለማመዳቸው ተግባራት

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

## በየቀኑ ለ20 ደቂቃ ያህል አብራችሁ አንብቡ።

| | የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት | ሒሳብ | ሳይንስ | ማህበራዊ ሳይንስ | የማበልጸጊያ ተግባር |
|---|---|---|---|---|---|
| **የበልግ ወቅት** | በእያንዳንዱ ቀን በንባብ ላይ ምን ያህል ጊዜ እንዳሳለፉ መመዝገቢያ ያዘጋጁ! ከእያንዳንዱ ታሪክ የወደዱትን ገጸ ባሕርይ በመዘርዘር ገጸ ባሕሪው እርስዎ ያደነቁለትን ብቃት ያሳየበትን የታሪኩን ክፍል ይለዩ።<br>•••<br>ተማሪዎ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ጎልማሳ ሰዎችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ ስለ አስተዳደግ ተሞክሮዎቻቸው እንዲማሩ ያድርጉ። ተማሪዎ የራሱን ሕይወት ቃለ መጠይቅ ከሚያደርጉት ሰው ሕይወት ጋር እንዲያነጻጽር ይጠይቁት። | ገበያ በሚወጡበት ወቅት ዋጋዎችን ያስሉ። ለተማሪዎ "እነዚህ ዕቃዎች በድምር ስንት ያወጣሉ? መልሴ ስንት ነው? ሂሳቡን እኩል ከከፈለነው እያንዳንዱ ወገን ስንት ይከፍላል?" የሚሉ ጥያቄዎችን ያቅርቡ<br>•••<br>ወደ ውጭ በሚወጡበት ወቅት ሰዎችና እቃዎችን ለመግለጽ የጥምርታ ቋንቋን ይጠቀሙ (ለምሳሌ፡ የ Redskins ደጋፊዎች ከ Cowboys ደጋፊዎች ያላቸው ጥምርታ 5 ለ 3 ነው)።<br>•••<br>ልጅዎ የተለያየ መጠን ያላቸው ጥራጥሬዎችን የነጠላ ዋጋ በማስላት የተሻለ ዋጋ እንዲወስኑ ያድርጉ (ማለትም፡ $21.7 ፓውንድ ካርቶን ያለው የፍራፍሬ ሉፕ በ $3.84 መግዛት $12.2 ፓውንድ ካርቶን የፍራፍሬ ሉፕ በ $2.75 ከመግዛት የተሻለ ነው? ለምን? | ስለ አልበርት አንስታይን ልጅዎን ያስጎብኙ ፕላኔታሪዩም ስሚዝሶኒያ ብሄራዊ አየር እና የህዋ ሙዚየሞች ያስጎብኙ፡፡<br>•••<br>ልጅዎን ወደ Smithsonian National Museum of Natural History የቅሪተ አካላት ማሳያ አዳራሽ በመውሰድ ሕይወት በምድር ላይ እንዴት እንደጀመረ፣ የዳይኖሰሮች ዘመን እስከ ከከፍተኛ የፕላኔት ለውጦች ጊዜ ድረስ ተመልከቱ። | ከተማሪዎ ጋር ሆነው በኮሙኒቲዎ ዙሪያ የእግር ጉዞ በማድረግ ተማሪዎ በኮሙኒቲ ፕሮፋይል ካርታው ላይ የሚያሳዩት የአካባቢ የመረጃ ምንጮችን እንዲለይ ያግዙት። ከልጅዎ ጋር በትራንስፖርት ሲጓዙ ካርታዎችን ማንበብን ይለማመዱ (በሜትሮ ውስጥ፣ በ GPS/Google ካርታዎች ላይ፣ ወዘተ…)።<br>•••<br>በዕለታዊ ሕይወታችን ውስጥ የምንጠቀምባቸው ነገሮች ለምሳሌ ልብስ፣ መኪኖችና ምግብ ከየት እንደሚገኝ በማወቅ ተማሪዎ በመላው ዓለም ዕቃዎች ከየት እንደሚመጡ እንዲገነዘብ ያግዙት። ሃገራት በመተባበር እንዴት ያለቀለት ምርት እንደሚያወጡ ይወያዩ። | ብሔራዊ መካነ እንስሳትን ይጎብኙ! የሚወድዷቸውን እንስሳት ምልከታዎችን ይመዝግቡ (ቀለም፣ ቅርጽና መጠን)። ምልከታዎችዎ በተቻለ መጠን ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያድርጉ። ለምሳሌ፣ "አንበሳው ጠይምና ጠንካራ ነው።"<br>•••<br>ወደ National Mall የጉዞ ዕቅድ ያውጡ! ከሐውልቶች ወይም የማስታወሻ ሕንጻዎች መካከል የአንዱን ታሪክ ይዳስሱ። ሐውልቱ ለእርስዎ ምን ትርጉም እንዳለው ተወያዩ። |
| **የክረምት ወቅት** | ከልጅዎ ጋር አብረው በመሆን የግል ማንነታቸውንና ለየት የሚያደርጋቸውን ችሎታዎች ይለዩ፣ ቅርስ የአንድ ሰው ማንነት አካል ነው። | ልጅዎ እይታዊ ፓተርን እንዲቀጥልና በ43ኛው ፓተርን ውስጥ ምን ያህል ነገሮች እንደሚኖሩ ይናገር ዘንድ ይጠይቁት። ምን ያህል ነገሮች በፓተርኑ የትኛውም ሒደት ውስጥ እንደሚኖሩ ለመወሰን ኢኩዌዝን መፍጠር መቻላቸውን ይመልከቱ። http://www.visualpatterns.org/ ይመልከቱ | ልጅዎን ወደ Smithsonian National Museum of Natural History's Hall of Geology, Gems, and Minerals ለጉብኝት በመውሰድ የመሬት የከበረ ድንጋይ፣ ማዕድናት፣ አለቶች፣ የመሬት መንቀጥቀጥና እሳተ ገሞራ ሚስጥሮችን እንዲማር ያድርጉ። | "I am Malala" ነኝ የሚለውን መጽሐፍ በአቅራቢያችሁ ካለ ቤተ መጻሕፍት በመዋስ አብራችሁ አንብቡት።<br><br>ልጅዎ ለዲሲ የከተማ ልማት መመሪያ የሚጽፈውን ደብዳቤ እንዲያጋራ በመጠየቅ የከተማ ኑሮ በጊዜ ሒደት እንዴት እንደተቀየረ በሚደረግ ውይይት ላይ ይሳተፉ። | ወደ bit.ly/TypingFun በመግባት አዝናኝ ጨዋታዎችና ተግባራትን በመጠቀም በኮምፒዩተር ላይ የመጻፍ ፍጥነትዎን ያሻሽሉ። ሁሉንም ጨዋታዎች ማሸነፍ ይችላሉ? |
| **የፀደይ ወቅት** | በአፈ ታሪኮችና እውነት ላይ ያልተመሰረቱ ገጸ ባህርያት ላይ ተመስርተው ፊልም ይመልከቱ። ገጸ ባህርያት ከፊልም ይልቅ በመጽሐፍ ውስጥ በተለየ መልኩ እንዴት እንደቀረቡ ያስረዳ ዘንድ ልጅዎን ይጠይቁ። | በዘወትር ሕይወት ውስጥ ያሉ ቅርጾችን በመለየት ቅርጾችን ወደ አራት ማዕዘንና ሶስት ማዕዘን እንዴት እንደሚከፋፍሉ ይወያዩ።<br>•••<br>ልጅዎ በዘወትር ሚድያ (ጋዜጣ፣ ቲቪ፣ ማህበራዊ ሚድያ፣ ወዘተ…) ከሚሰጥ ዳታ ውስጥ እንዲሳተፍ ይጠይቁ። ማሳያው ለሚታየው ዳታ የተሻለ መሆኑን፣ ዳታው ምን እንደሚጠቁም፣ ዳታውን እንዴት ማጠቃለል ወይም የዳታውን ቅርጽ እንዴት መግለጽ እንደሚቻል ተወያዩ። | በበጋ ወቅት የሽርሽር ዕቅዶችዎ ውስጥ ልጅዎን ያካትቱ። ሊሄዱ የሚችሉባቸውን ቦታዎች ያስቡ፣ ሊጎበኙት የሚፈልጉትን ቦታ የአየር ፀባይና የአየር ሁኔታ በተመለከተ በጋራ መረጃ አፈላልጉ። ለመጎብኘት ከወሰኑ፣ ማስቀረት ወይም መዘጋጀት ያለብዎት እጅግ አስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ምንድን ነው? | ልጅዎ በአፍሪካ ውስጥ ስላሉ የተለያዩ ሃገራትና ክልሎች ብዝሃዊነት ምን እንደተማረ ይጠይቁ።<br>•••<br>የ SAGE ድሕረ ፈተና በጁን ወር ላይ ይደረጋል! ልጅዎ የቻለው ሁሉ እንዲያደርግ ያበረታቱት! | Kenilworth Park and Aquatic ይጎብኙ። ዘወትር ቅዳሜና እሁድ በ10 a.m. በኩሬው አካባቢ እንቁራሪቶችን ይፈልጉ። ለተጨማሪ መረጃ nps.gov/keaq ይጎብኙ። |

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት ሒሳብ ሳይንስ ማህበራዊ ሳይንስ የማበልጸጊያ ተግባር